EthioLion

# በልተኸው ተቀደስ

ሃቁ እንዳይታወቅ ፣ ለእውነት መስካሪ ፣ አንደበት ታፍና
ላገር ልዕልና ፣ ለነጻነት ትግል ፣ እያልን ደፋ ቀና
ትግልን ያስመቱ ፣ ሰው ከነ ህይወቱ ፣ ገደል የጨመሩ ፣ ተግባር ተረሳና
ለእውነት ፣ ስለ እውነት ፣ ላገሩ የሚታገል ፣ ታጋይ ሰው ጠፋና
በተገንጣይ አሸከር ፣ የሰላይ ቅጥረኛ ፣ ልክ እንደ ካቻምና
ልበ ሙቅ ቀልባሾች ፣ ይጫወቱብናል ፣ ዛሬም እንደገና
ከገንጣይ አብረው ፣ አገርን ሊያፈርሱ ፣ ባንድነታችን ላይ ፣ ተነስተዋልና
በነ ተንሸራታች ፣ በጎጠኞች ሴራ ፣ ጥያቄ ሳይገባ ፣ ያገር ህልውና
ተምረው ደንቆሮ ፣ ተሹመው አጥፊዎች ፣ ተመስክሯልና
ገንጣይና አድር ባይ ፣ ከወያኔ መንጋ ፣ አይሻሉምና
ደም ተገብሮበት ፣ አጥንት ተከስክሶ ፣ ትግል እንዳይሆን መና
ታግለን ካልጣልናቸው ፣ ነጻነት አይመጣ ፣ አይወርድ እንደመና
ይጧጧፍ ትግላችን ፣ በግራም በቀኝም ፣ ይንደድ ይጋምና ።

ጥንት የምናውቃቸው ፣ ካንዴም ሁለት ሶስቴ ፣ ድርጅት የከዱ
የሞቀ አራጋቢ ፣ አጎብድዶ አዳሪ ፣ መሸጥ የለመዱ
በየፌርማታው ላይ ፣ አቋም የለወጡ ፣ ህዝብን የሸውዱ
ትላንት ስልጣን ይዘው ፣ ገደል የጨመሩ ፣ በጭካኔ ያረዱ
ከነሱ ተቃቅፎ ፣ ትግል አይገፋም ፣ ይብቃ ማሸርገዱ
የሚጠፋው አገር ፣ ሟቹም የሰ ልጅ ነው ፣ በደም አይቀልዱ
በጭቁኑ ሕዝባችን ፣ ማላገጡ ይብቃ ፣ ከጫንቃው ይውረዱ
በተበላ እቁብ ፣ ዛሬም በኪሳራ ፣ ይቁም መነገዱ ።

ካፍንጫው በልራቀ ፣ ማሰብ በማይችለው ፣ ቢሞካሽ ቢወደስ
የአቶ ግርግሩ ፣ ሥልጡን ፖለቲካ ፣ አገር እንዳያፈርስ
አበላ ባይ ሆዳም ፣ የስልጣን ጥመኛ ፣ ሲሮጥ ሲልከሰከስ
የቀን ጅብ ነውና ፣ ሳታስበው መጥቶ ፣ ሳይዘነጥል ሳይነክስ
ቢከረፋም እንኳን ፣ ጅቡ ከሚበላህ ፣ በልተኸው ተቀደስ
ካገርህ አይበልጥም ፣ የገንጣይ አስገንጣይ ፣ ጩኸትና ማልቀስ ።

ታዛቢው ... April 25, 2011

Ethiopia will prevail!